# ነገረ ማርያም

## ታቦተ ጽዮን

ከሃብተ ሥላሴ ዳኛቸው

የታቦት የት መጣው ከእሥራኤል ሕዝብ የነፃነት ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው።

በሰው ልጆች የታሪክ ጉዞ ውስጥ በአስከፊ ገጽታው እየተመላለሰ የማኅበረሰብን ኑሮ በሚያገለባብጠው ድርቅና ረሃብ ምክንያት ከከነዓን ወደ ግብፅ የተሰደዱት ዕብራውያን /የአብርሃም/ ልጆች 430 ዓመታት ያህል በባርነት ተገዝተው ከኖሩ በኋላ ከመጠን ያለፈው ጭቆናቸው፣ ከሥፍር የተረፈው ሥቃያቸውና ያለማቋረጥ የፈሰሰው ዕንባቸው ቅድመ እግዚአብሔር ደርሶ፣ ነጻ ወጥተዋል። ወደ ምድረ ርስት ተመልሰው ለመግባትም ሌላ ዓርባ ዓመት፣ በበረሃ በምድረ በዳ የቃሉ ኑሮ ኳትነዋል።

ይህ ሁሉ ሲሆን በእምነት ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው የቀረበ ግንኙነት ያልተቋረጠ በመሆኑ የእግዚአብሔር ርዳታና ቸርነት አልተለያቸውም፣ በፈጣሪ የፍትሕ ሚዛን፣

ከባርነት መዳፍ ፈልቅቆ ለማውጣት በጨቋኞቻቸው ላይ ከወረደው ልዩ ልዩ ቅጣትና መቅሰፍት ሌላ ባሕር ከፍሎ አሻግሮአቸዋል፣ ቀን በሐሩር ፀሐይ /በዋዕይ/ እንዳይቃጠሉ የሚከልላቸው ደመና፣ ሌሊት የሚመራቸው የብርሃን ዐምድ ታዞላቸዋል። በዚህም የኃይል ተአምራት ከተከታታይ ጠላትና ከበረሃው የጉዞ ጠባይ ከሚነሱ ልዩ ልዩ ፈታኝ ችግሮች ተጠብቀዋል። /ዘፀ.፲፫፡፳፩-፳፪/ ከሰማይ የተገኘውን ኅብስት /መና/ ተመግበዋል፣ በእግዚአብሔር ከሃሊነት የተዘጋጀ ሥጋ ተትረፍርፎላቸዋል፣ ከሚንበለበል ምድረ በዳ ይገኛል ተብሎ የማይገመት ቅዝቃዜና ድሩቅ /ጥሬ/ ውሃ ከአለት /ከምንጭ/ እየመነጨላቸው /እየፈለቀ/ ጠጥተዋል። /ዘፀ.፲፯፡፲፫/

ለሕይወታቸው ከሚሹት ነገር ሁሉ የተጓደለባቸው ምንም አልነበረም በዚያው አንጻር ደግሞ ከእምነቱ መስመር ባፈነገጡና ረድኤቱን እየዘነጉ በጥጋብ መንፈስ በመነሳሳት በእግዚአብሔር ላይ ማንጐራጐር በፈጠሩ ቁጥር ተግሳጽና ቅጣት ጐብኝቷቸዋል። አንገብጋቢ መርዝ ባለው የበረሃ እባብ ተነድፈዋል፣ በሰይፍ፣ በለምጽና በልዩ ልዩ መቅሰፍት ተመተዋል። በጦርና በምርኮ፣ በአባርና ቸነፈር ተቀጥተዋል። የስነፍጥረት ሕይወቱ ፈጣሪው ነው። እያንዳንድ የፍጥረት ወገን ሲዋኝ የሚኖረው በፈጣሪው የምግብና ዓለም ውስጥ ነው የፈጣሪው ምግብና /ጸጋና ረድኤት/ ከተለየው ከውሃው የተለየ ዓሣ ነው ሕዝብ እግዚአብሔር የተባሉ እሥራኤል ቅጣት ይደርስባቸው የነበረው ከእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት በወጡ ጊዜ ነበር። እግዚአብሔር በመልኩና ምሳሌው ቀርጾ በተድላ ገነት ያኖረውን አዳምን ይጠብቀው፣ ዕለት ዕለት ይጐበኘውና ቃል በቃልም ያነጋግረው ነበር።

የሕይወት ስብራት ያገኘው ምድራዊ ጌትነትን በሰማያዊ ዙፋን ለመለወጥ የጠላትን የተሳሳተ ምክር በመስማት ጆሮውን አንቅቶ ወደ ሰማይ ባንጋጠጠ ጊዜ ነው በስሕተቱ የእግዚአብሔር ጸጋ የተለየው ከረድኤቱ ተራቆተ። ሕይወቱ ከቁም የወደቀ ሸክላ ሆነ። ተሰበረ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በፊቱ የሚሄድ፣ የሚያየው፣ የሚዳስሰውና የሚያነጋግረው አምላክ ለማግኘት ሲሻ ሲመረምር ኖረ። በተፈጥሮ ከሱ በላይ ኃይልና ጉልበት አላቸው ብሎ የገመታቸውን ነገሮች ሁሉ፣ ዛፉንና ተራራውን፣ ወንዙንና ኸረቱን፣ እንስሳቱንና አራዊቱን፡ ፀሐይንና ጨረቃን በአምልኮ ደረጃ ሲያለዋውጣቸው ኖረ፣ የጣኦት አምልኮ፣ የጨለማና የዳበሳ ዘመን አሳለፈ።

አምላክ እሥራኤል የህዝቡን እምነት ሊያጸናላቸው ፈቃዱ በሆነ ጊዜ በሲና ተራራ ለሙሴ ተገልጾ የቃል ኪዳንና የመታዘዝ ምልክት የሚሆኑ አሥር ትእዛዛት /ሕግጋት/ የተጻፈባቸው ሁለት ጽላቶችን /ሰሌዳዎችን/ ሰጥቶአቸዋል። ለእነሱም ማደሪያ /ማስቀመጫ/ ታቦትና እንደመቅደስ የምታገለግል የምስክር ድንኳን እንዲሰራ ነቢዩ ሙሴን አዞታል። አሰራሩንም አሳይቶታል፣ ይህንንም «አርአዩ ለሙሴ ግብራ ለደብተራ እግዚአብሔር ለሙሴ የምስክር

### አይዞህ ትለኛለች

ሆዱን ሆድ ሲብሰው
አልችል ሲል አንጀቱ
ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ
ሲርድ ሰውነቱ
ባዶነት ሲሰማኝ
ጠፍቶኝ እኔነቴ
ስሟን ባነሳሳ
ስላት የአንጀቴ እናት
በጣም ተጨንቄ እሷን በማጸናናት
ባለቅስ ስተክዝ
ስወድቅ ከደጇ
አይዞህ ትለኛለች
ድንግል ከነልጇ።
ያሬድ ግልማ አ.አ


ድንኳንን አሰራር አሳየው» በማለት ቅ/ያሬድ በዜማ ምስጢሩን አድንቆ ገልጾታል። ከኦሪቱ ድንኳን ተያይዞ በመጣው ትውፊት ሰሎሞን ለታቦተ ጽዮን ማደሪያ ለእግዚአብሔር ስም መመስገኛ ቤተ መቅደስ ሠርቷል።

ዐሰርቱ ቃላት /ሕግጋት/ የተጻፈበት /ሰሌዳ/ ጽሌ በብዛት ሲነገር ጽላት፣ የዚህ ማስቀመጫ ወይም ማደሪያ ታቦት ይበላል። ታቦት መታያ መገለጫም ነው አምላክ እሥራኤል ለሕዝቡ በምሕረትና በረድኤት የሚገለጥበት ስለሆነ ነቢዩ ሙሴ፣ ይህችን የቃል ኪዳን ሕግ ለመቀበል ተጠርቶ በሲና ተራራ በቆየበት ጊዜ «በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሰራልን» በማለት አሮንን ያስገደዱት ሕዝበ እስራኤል ፍላጎት ከዚሁ የተነሳ እንደነበር ያመለክታል። የፍጡር ኅሊና ዕረፍት የለውም አለ ሲባል የሚሰማውን ነገር ሁሉ ሊያየው፤ ሊሰማው ሊቀምሰው፣ ሊያሸተውና ሊዳስሰው በስሜት ሕዋሳቱ ሁሉ ይፈልጋል።

ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበላቸው ጽላት (ገበታዎች) ከአዳም ሕይወት ጋር ተያይዞ የሚተረጐም ረቂቅ ምሳሌና ምስጢር አላቸው። ከእግዚአብሔር ጋር ከቆየበት ተራራ በተመለሰ ጊዜ እንዳስቀመጠው ያልተገኘው ሕዝብ በጉሽ ጠጅ ተሳክሮ በጣኦቱ ዙሪያ ሲጨፍርና ሲያጨበጭብ ስላገኘው ደንግጦ /ተቆጥቶ/ የሰበራቸው ሁለቱ የቃል ኪዳን ጽላት /ገበታዎች/ የአዳም ምሳሌዎች ነበሩ። የወደቀው፣ የተሰበረውና የደቀቀው ሕይወቱ፣ የስጋውና የነፍሱ፣ በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ የመፈረዱ ምሳሌ ነበር።

ሕጉ ቢጠብቁት የሚጠብቅ ስለሆነ ታቦተ ኪዳንን ሕግ ይለዋል። ሕጉን ለሚጠብቁና ትእዛዙን ለሚፈጽሙ ተካሂዶበታል።

ያች አስሩ ቃላት በአጻብዓ እግዚአብሔር (በግብር አምላካዊ) የተጻፈበት እንደሆነች፣ አሥሩ ቃላትን በጽላቱ ጽፎ በመስጠቱ በኋለኛው ዘመን ሰው የመሆኑን ምስጢር



የነገረን፣ ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር በአጻብዓ መንፈስ ቅዱስ ተቀርጾ በማሕፀነ ድንግል ተገኝቷል። ከንጽሕት እመቤታችን ከድንግል ማርያም ሰው ሆኖ ተገልጾአል።

ከእግዚአብሔር ፍቅር መለየት፣ ከአምልኮቱ መራቅና የማያዛልቅ ጉዞ መጀመር አደጋ ነው።

ከግብፅ ባርነት ነጻ ያወጣውንና ቀን በደመና ሌሊት በብረሃን ዐምድ እየጋረደ ኅብስተ መላእክትን እየመገበ የመራውን ፈጣሪውን ጨክኖ በመካድ ለጣኦት አምልኮ የተንበረከከው፣ በፍቅሩ የሰከረውና የተሳሳተ አቅጣጫ የተከተለው ሁሉ ተፈጭቶ የተበጠበጠውን የጣኦት አተላ እያንገሸገሸው ተግቶታል። ወንድም በወንድሙ፣ አባት በልጁ ወገን በወገኑ ላይ እንዲነሳበትና እንዲተላለቅ በታዘዘው የሰይፍ መጨፋጨፍ የጣኦት ፍቅር መለያ ሆኖ በየግንባሩ ላይ የለምጽ ምልክት ከተፈነጠቀባቸው ወገኖች በሺህ የሚቆጠር ብዙ ሕይወት ወድቆበታል። በከይሲ (ዲያብሎስ) የተሳሳተ ምክር በምኞት አሽክላ (አሽክት) ተጠልፎ የወደቀው የአዳም ዘር ሁሉ በመረገሙ እሾህና የአሜከላ (ኩርንችት) ባበቀለች ምድር ፳፻ ዘመን የፍዳ ጽዋውን ሲጋት ኖሯል።

«ቀር ከመ ቀዳምያት እንደመጀመሪያዎቹ አድርገህ ጽላቱን ቅረጽ (ሥራ)» ተብሎ የታዘዘው ሙሴ የቀረጻቸው ሌሎች አዳዲስ የቃል ኪዳን ጽላት የአማናዊት ታቦት የቅድስት ድንግል ማርያም የነፍሷን የሥጋዋ /ምሳሌ ሆነው የተሰሩ ነበሩ። በመጀመሪያው ሰው (አዳም) የተሰበረው፣ ሕይወት በማይጠፋ የታደሰባት «እውነተኛ ጽሌ እመቤታችን ናትና ወሐደስኮ በዘኢ ይማስን ወብኪ ተሐደሰ ቀዳሚ ኩሉ ፍጥረት» (ኪዳን ቅዳሴ ማርያም) ተብሎ የተጻፈውም ለዚህ ነው።

ምን ጊዜም ቢሆን፣ ነቢያት፣ መምህራን መሪ አስተማሪ ከሌለው፣ የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት ከተለየው የሰው ሕይወት ራቁት ነው። ይቅበዘበዛል፣ ራሱን፣ ሃብቱን፣ ጉልበቱን ወይም ሌላ ያዋጣኛል ብሎ የሚያስበውን ነገር ወደ ማምለክ ያዘነብላል። መጨካከን፣ መተላለቅና የዋይታ ዘመን የሚወለደው ያን ጊዜ ነው።

ቃል ኪዳን የማይለወጥ፣ የማይሻር፣ የማይፈታ የሕይወት ትስስር (ሰንሰለት) ስለሆነ የቃል ኪዳን (የሕግ) መግለጫ ሆነው የተ ሰጡት ጽላተ (ገበቶች) ተሰብረው አልቀሩም፣ ከማይነቅዝና ከማይ በላሽ እንጨት ሸምሸረሰጢን ግራር እንደገና ተቀርጸው (በይቀጥላል) እንዲሰሩ ታዞአል ተደርጓል። በጽላት ሙሴ የተመሰለች «የሙሴ ፅላት» የተባለች የአማናዊት ድንግል ማርያም ምሳሌዎቿ ናቸው። ያ የማይለወጥ ኪዳን እንዳለው ሁሉ ከሷ በተገኘው ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ የዘለዓለም ሕይወትን የሚያወርስ የማይለወጥ ጌታ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለታቦት ሕግና ሥርዓት ኪዳን የምትከተለው ትምህርት በዚህ መልኩ የተራቀቀ ምሳሌና ትርጉም ያለው የማይለወጥ የቃል ኪዳን መሰረት ነው።

ጽዮን አምባ፣ መጠጊያ ማለት ነው።

ጽዮን በስሟ አንጻር ሕዝበ እስራኤል (አይሁድ) የሚጠሩበት ኢየሩሳሌም ናት። የበደሉ ወደሷ ሸሽተው እርቅ፣ ሰላም፣ ምሕረትና ይቅርታ የሚያገኙባት፣ የተበደሉ ተጠግተው የሚጠቀሙበት ለጠላት የማትበገር /የማትደፈር/ አምባ የዳዊት ከተማ።

የዘለዓለም ሕይወት የተገኘባት ዮገረ እግዚአብሔር የተባለች የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ናት። ለኢየሩሳሌም ሰማያዊትም አምሳልና መርገፍ ሆና ትነገራለች። ኢየሩሳሌም ሰማያዊት በጥንተ ፍጥረት ታላቅ መልአክ ቅሩበ እግዚአብሔር አኀዜ መንጦላዕት የነበረው ሳጥናኤል የተፈጠረባት፣ ኋላ እሱ በግብሩ ሲተዋት ለአዳም የተሰጠች የጌታ ክብር ወራሾች የምእመናን ቦታ ናት። «ታቦት ዘዶር» በመባል የምትታወቅ የክርስቶስ ማደሪያ የሆነች የድንግል ማርያምና የምእመናን ምሳሌ የሆነች የብረሃን ታቦት የተተከለባት ደገረ ቅዱሳን ናት። /ገላ ፬ ፡ ፳፮፣ ዕብ. ፲፪፡ ፳፪ ራዕ. ፲፭፡ ፲፱/

# በአታ ለማርያም

በተዋሕዶ እምነታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም በምናምነው እመነት ሌሎች ከሚቀበሉትና ከሚያምኑት ልዩ ከሚያደርጉን ዐብይት ነጥቦች፣

- ንጽሕተ ንጹሐን ድንግል ማርያም ከፍጥረት አስቀድሞ በአምላክ ሕሊና ታስባ የኖረች፤

- በጥፋት መርገም ከአዳም የወረደ የዘር ኃጢአት ያልተላለፈበት ቅድስተ ቅዱሳን፣

- አሥራ ሁለት ዓመት በቤተ መቅደስ ማደጓ፣

- በንጽሕና የተዘጋጀች፣ በቅድስና ያጌጠች ቅድመ ጸኒስ፣ ጊዜ ጸኒስ፣ ቅድመ ወሊድ ድኀረ ወሊድ በፍጹም ድንግልና የጸናች ማሕተመ ድን ግልናዋ የማይለወጥ ዘለዓለማዊት ድን ግል መሆኗን ማመንና ማስተማር ነው።

የዓለማት ፈጣሪ ልዑል እግ ዚአብሔር «በልዕልና ሆኖ ተመ ለከተ፣ ሁሉ እንደፈረሰ ጀሮ፣ እንደ ጦር ጐረሮ ተስተካክሎ በደለ፣ በጐ ነገርን የሚሠራት የለም» (መዝ.52) ተብሎ በተነገረበት ትውልድ በአዳም ዘር መካከል በእሾህ ውስጥ እንደአጌጠች ጽጌረዳ በመዓዛ ቅድስና የተጠበቀች ንጽሕ ነፍስ፣ ንጹሕ ሥጋን፣ ንጹሕ ልቡናን ይዛ የተገኘች የንጉሥ ክርስቶስ መቅደስ ድንግል ማርያም ከሁሉ ትበልጣለች፣ ከሁሉም ትከብራለች «መልዕልተ ፍጡራን፣ መትሕተ ፈጣሪ» ናት። ከፈጠራት ጀምሮ ሥጋዊ አሳብ በሕሊናዊ ያልተመላለሰ ከሐልዩ፣ ከነቢብ፣ ከገቢር የነጻች እናትነትን ከድንግልና አስተባብራ የተገኘች የደናግል መመኪያ ናት።

«ልጄ ሆይ ስሚ፣ ምክሬን አድምጪ ንጉሥ (ክርስቶስ) ማደሪያው ልትሆኚ ደም ግባትሽን (ቅድስናሽን) ወዶአልና ዘመድሽን ርሺ» (መዝ. ፵፬፡ ፲) ተብሎ በነቢይ እንደተነገረ ለናትና አባቷ የብፅእት ልጅ የሆነችው ድንግል ማርያም ሆዷ ዘመድ ሳይወድ፣ አፏ እህል ሳይለምድ ከእናቷ እቅፍ ተወስዳ ሥላሴን እንደአባት እንደእናት መላእክትን እንደእህት እንደወንድም አድርጋ በቤተ መቅደስ ያደገች «እህተ መላእክት» ናት።

ልጆችን ለቤተ እግዚአብሔር መስጠት በቤተ መቅደስ እግዚአብሔ ርን እያገለገሉ እንዲያድጉ ማድረግ የልጅ በረከት ለማግኘት የሚናፍቁና እግዚአብሔርን ደጅ የሚጠኑ አማንያን እምነትና ልማድ ነው። እንሳሙኤልን የመሳሰሉ ነቢያት ሁሉ በቤተ መቅደስ ያደጉ ናቸው።

እመቤታችን ድንግል ማርያም ከሦስተኛ ዕድሜዋ ጀምሮ በግብር አምላካዊ ከሰማይ የተገኘ ሕብስትን እየተመገበች፣ ከሰማይ የተገኘ መጠጥን እየጠጣች ሐርና ወርቅ እያስማማች እየፈተለች በመላእክት ሞግዚትነት በቤተ መቅደስ ያደገች፣ በንጽሕና በቅድስና የተሸለመች የሰማይና የምድር ፈጣሪ ማደሪያ /ታቦት/ ናት። ንጽሕተ ንጹሐን ድንግል ማርያም እንደ ዓለም ሴቶች ልጆች በሳቅና ስላቅ፣ በቧልትና ጨዋታ ያደገች አይደለችም።

ቤተ መቅደስ የገባችበትና መልአኩ ፋኑኤል በአንድ ክንፉ ሕብስትና ጽዋዕ አቅርቦ አንድ ክንፉን ጋርዶ በመመገብ ቤተ መቅደስ ቆይታዋ በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑ የተረጋገጠበት ታኅሣሥ ፫ ቀን በየዓመቱ በቤተ ክርስቲያናችን በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ይከበራል። በዔሊ ልጆች ኃጢአትና በደል በምርኮ ቆይታ በኃይል ተአምራት የተመለሰችው ታቦተ ጽዮን ወደ ቤተ መቅደስ እንደተመለሰች ሁሉ አማናዊት ታቦት ቅድስት እመቤታችንም በናትና አባቷ ቤት ሦስት ዓመት ከኖረች በኋላ ወደ ቤተ መቅደስ ገብታለች። «በአታ ለማርያም» ማለት የማርያም ቤተ መቅደስ መግባት ማለት ነው።

ወሰብሐት ለእግዚአብሔር